# የብልጽግና ፓርቲ
# የአመራር ምዘና ማስፈጸሚያ
# መመሪያ

# መግቢያ

- የብልፅግና ፓርቲ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልጽግና የማረጋገጥ ርዕይን እውን ለማድረግ
  - ✓ በአስተሳሰባቸው
  - ✓ በስነ ምግባራቸው፣
  - ✓ በእውቀታቸው፣
  - ✓ በክህሎታቸውና
  - ✓ በአፈፃፀም ብቃታቸው የላቁ አመራሮችን ቀጣይነት ባለው የውስጠ ፓርቲ አመራር ሥርዓት መፍጠር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል።

# ዓላማ

- **የመመሪያው አላማ የአመራር አፈጻጸም ምዘና ውጤትን መሰረት ባደረገ እና አሳታፊ፣ ግልጽ፣ ወጥና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ በማስፈጸም የፓርቲውን አመራር ጥራትና ውጤታማነት ማሳደግ ነው።**

**የአመራር ምዘና በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-**

- የአመራር ምዘናው እውነተኛ መረጃና አስፈላጊ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፣
- የአመራር ምዘናው አሳታፊ፣ ፍትሓዊ፣ ግልጽ፣ ወጥነት ያለውና፣ ከወገንተኝነት እና ከቡድንተኝነት የፀዳ መሆን ይኖርበታል።
- ምዘናው አመራሩ ወደ ራስ/ውስጥ እንዲመለከት፣ ጥራትና ጥንካሬውን የሚያሳድጉ ገንቢ ሃሳቦችን ከሥራ ባልደረቦቹ እንዲያገኝ እና በውስጡ ቁጭት በመፍጠር ለቀጣይ ስራ የሚያነሳሳው መሆን አለበት።
- የአመራር ምዘናው የሕዝብ ወገንተኝነትና ተጠቃሚነትን የበለጠ የሚያረጋግጥና የፓርቲውን ቅቡልነት የሚያሳድግ መሆን ይኖርበታል።
- የአመራር ምዘናው አመራሩ የፓርቲ ዲሲፕሊን እና አንድነትን ጠብቆ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ የሚያስችልና ግንባር ቀደሞችን ለማብዛት የሚያግዝ እንዲሁም ግድፈት የታየባቸውን ለማረም፤ አልታረም ያለውን ደግሞ ከኃላፊነት ለማሰናበት የሚረዳ መሆን አለበት።

# የአመራር አፈፃፀም መመዘኛ ነጥቦችና የሚኖራቸው ክብደት

– የብልጽግና ፓርቲ አመራር ምዘና ውጤት የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች እና የመደበኛ ሥራዎች አፈጻጸም ምዘና ውጤት ድምር ይሆናል።
– የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች ምዘናው ከአጠቃላይ የአመራሩ ምዘና ውጤት የሚኖረው ድርሻ 30% ይሆናል።
– ከ30% የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች ምዘና ውስጥ 10% አመራሩ እራሱን የሚመዘን ሲሆን ቀሪው 20% በስራ ባልደረቦቹ የሚመዘን ይሆናል።
– የአመራሩ የመደበኛ ሥራዎች አፈጻጸም ምዘናው ደግሞ ከአጠቃላይ ውጤቱ የሚኖረው ድርሻ 70% ይሆናል።
– የአመራሩ የመደበኛ ሥራዎች አፈፃፀም ምዘና መሰረት የሚያደርገው እያንዳንዱ አመራር በተመደበበት ተቋም ከ10 አመቱ እቅድ ተቀድቶ በተዘጋጀው አመታዊ እቅድ ላይ ይሆናል።

# የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች አፈፃፀም የምዘና መድረኮችና የውጤት አሰጣጥ ሂደት

- የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በጋራ መድረካቸው የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች አፈፃፀም ምዘና የሚያከናውኑ ይሆናል።
- ሌሎች አመራሮች በየደረጃው ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ በሚዘጋጁ የምዘና መድረኮች የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች አፈፃፀም ምዘናቸው የሚከናወን ይሆናል።
- በእያንዳንዱ የአመራር ምዘና መድረክ የአመራሩ የተናጠል የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች ምዘና ከመካሄዱ በፊት በአጠቃላይ አመራሩ በመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ያለበትን የወል ደረጃ የሚያሳይና በግለሰብ ደረጃ ለሚደረገው ምዘና ግብዓት የሚሆን የአካል ግምገማ ይደረጋል።
- የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች ምዘና መድረኩ ተሳታፊዎች/የሥራ ባልደረቦች በተመዘኙ አመራር የቀረበውን የራስ ምዘና ውጤት መነሻ በማድረግ ስለ ተመዘኙ አመራር ያላቸውን አስተያየትና የምዘና ሃሳብ ያቀርባሉ።

## የምዘና ሪፖርት ስለማጽደቅ እና ስለማሳወቅ

- የአመራር ምዘና ውጤት መዋቅሩን በሚመራው የአስተባበሪ ኮሚቴ አማካኝነት የሚፀድቅ ይሆናል።
- በየደረጃው ያለው አስተባባሪ ኮሚቴ የምዘና ውጤት አንድ ደረጃ ከፍ ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ ይጸድቃል።
- የክልልና የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ የምዘና ውጤት በብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት የሚፀድቅ ይሆናል።
- በየደረጃው በሚገኙ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የጸደቀው የአመራር ምዘና ሪፖርት በ3 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል መላክ ይኖርበታል።

## በምዘና ውጤት ላይ ተመስርቶ ስለሚሰጥ ደረጃና ውሳኔ

- አንድ አመራር በመደበኛ እና በውስጠ ፓርቲ ሥራዎች አፈፃፀም ድምር ውጤት ከ95% በላይ የሚያገኝ ከሆነ አፈጻጸሙ በጣም ከፍተኛ/የሞዴል አፈጻጸም ደረጃን የሚያመለክት ነው።
- ከ85% በላይ እስከ 95% የሚያገኝ ከሆነ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የአፈጻጸም ደረጃን የሚያመለክት ነው።
- ከ65% በላይ እስከ 85% የሚያገኝ ከሆነ አፈጻጸሙ መካከለኛ የአፈጻጸም ደረጃን የሚያመለክት ነው።
- ከ50% እስከ 65% የሚያገኝ ከሆነ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የአፈጻጸም ደረጃን የሚያመለክት ነው።
- ከ50% በታች ከሆነ አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው።

# የውስጠ ፓርቲ ሥራዎች መመዘኛ መስፈርቶች

- የአመለካከት ጥራት
- የአመራርነት ኃላፊነትን በብቃት መወጣትን በተመለከተ
- የአመራር ስብዕናና ስነ-ምግባር ከመላበስ አኳያ
- ሌሎች የፓርቲ አባልነት ግዴታዎችን መወጣት

# አመሰግናለሁ